

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከጃንዋሪ 1-31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

## እንዲሁም

## ከፌብርዋሪ 1-28 /2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ

## እና ምክረ ሃሳብ

ፌብርዋሪ 2026

አዲስ አበባ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1.1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ


ባለፈው የጃንዋሪ ወር በአብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፤ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል፡፡ በተለይም በመጀመሪያዎች ቀናቶች ላይ በሰሜን ምሥራቅ፣ መካከለኛው፣ ምሥራቅ እና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ነበራቸው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ በአብዛኛዉ ቀናቶች ላይ የተስተዋለ ሲሆን፤ በሰሜን ምሥራቅ፣ መካከለኛው፣ ምሥራቅ እና ደቡብ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧ፡፡ ለአብነትም አዲግራት 3.5፣ 4.5፣ 4.5፣ 3.5፣ ሐሮማያ 4.0፣ 4.6፣ 2.4፣ -3.4፣ 0.2፣ 1.8፣ 2.0፣ 3.0፣ 4.8፣ 2.8፣1.0፣ 1.2፣ 3.2፣ 0.4 አልም ከተማ 4.0፣ 3.8፣ 3.4፣ 2.5፣ 3.4፣ 3.2፣ 3.0፣ 4.0፣ 4.0፣ 4.2፣ 2.8፣ 2.5፣ 3.0፣ 3.8፣ 4.0፣ አምባ ማሪያም 4.5፣ 4.6፣ 4.5፣ 4.8፣ 3.6፣ ባቲ 4.6፣ 4.8፣ 4.0፣ 4.0፣ 3.0፣ 2.0፣ 2.0፣ በሀር ዳር 4.0፣ 3.8፣ 4.6፣ 4.0፣ ቡሂ 4.4፣ 2.0፣ 1.0፣ 3.0፣ 0.2፣ 1.4፣ 1.6፣ ኮምቦልቻ 4.6፣ 4.6፣ ደበረ ብርሃን 2.6፣ 3.0፣ 1.6፣ -0.4፣ 0.6፣ 3.8፣ 2.0፣ 3.0፣ 2.4፣ 3.6፣ ዳንግላ 4.8፣ 4.0፣ 3.5፣ 4.0፣ 4.5፣ 4.0፣ 4.7፣ ቢሾፍቱ 2.8፣ 2.1፣ 2.2፣ 3.2፣ 2.9፣ 2.5፣2.0፣ 3.2፣ 2.0፣ እነዋሪ 4.8፣ 4.5፣ እምድብር 4.6፣ 4.8፣ ጅግጅጋ 4.2፣ 3.0፣ 2.5፣ 0.5፣ 1.5፣ 0.5፣ 2.4፣ 2.5፣ 4.6፣ 3.0፣ 3.3፣ 3.2፣ ጅማ 4.4፣ 3.4፣ ማይጨዉ 2.5፣ 4.8፣ 4.6፣ 2.2፣ 2.8፣ መሃል ሜዳ 2.5፣ 4.8፣ 4.6፣ 2.2፣ 2.8፣ ሮቤ 4.3፣ 2.8፣ 0.6፣ 3.0፣ 3.2፣ 2.8፣ 3.0፣ ወግል ጤና 3.0፣ 2.5፣ 3.0፣ 2.5፣ 2.0፣ 1.5፣ 2.5፣ 2.2፣ 3.5፣ 0.5፣ 3.0፣ 4.0፣ ወረኢሉ 3.0፣ 3.5፣ ጉዶ በረት 3.5፣ 3.5፣ 4.5፣ 3.5፣ ኅቦያሬ 4.8፣ ዳባት 4.2፣ ኮሶበር 4.1፣ ጨለንቆ 2.1፣ -2.0፣ -2.0፣ -3.0፣ -4.0፣ 2.0፣ -1.0፣ -2.0፣ -3.0፣ -3.0፣ -1.0፣ 1.8፣ 1.2፣ 1.0፣ -1.0፣ 1.0፣ -1.0፣ 2.2፣ 2.0፣ -1.0 ቁሉቢ 4.5፣ 3.2፣ 3.0፣ 2.8፣ 3.0፣ 3.1፣ 2.5፣ 2.8፣ 2.6፣ 2.5፣ 2.4፣ 2.3፣ 2.1፣ 2.0፣ 3.8፣ 3.6፣ 3.5፣ 3.1፣ 2.3፣ 2.0፣ 2.2፣ ጨፌ ዶንሳ 3.7፣ 3.0፣ 3.0፣ 4.5፣ 2.5፣ ጋሸና 4.2፣ 4.9፣ 2.4፣ 2.3፣ 3.1፣ 2.3፣ 4.1፣ ኮራም 1.0፣ 1.0፣ 4.0፣ 4.5፣ 4.0፣ 3.0፣ 1.5፣ 2.5 ዉቅሮ 4.5፣ እንዲሁም መልካ ጀባዱ 4.0፣ 4.0፣ 4.0፣ 4.0 በዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል፡፡

በሌላ በኩል ባለፈው የጃንዋሪ ወር አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናቶች ላይ የተሻለ ገጽታ ነበራቸው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የደቡብ አጋማሽ እና የደቡም ምዕራብ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የተሸላ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በጥቂት የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ3 ሚ.ሜ በላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ5 ሚ.ሜ


በላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አማን 17.3፣ 11.7፣ 7.8፣ እምድብር 13.1፣ 5.7፣ 8.5፣ 15.5፣ አርጆ 12.8፣ ቡሂ 6.7፣ በደሌ 17.5፣ ብላቴ 15.7፣ ጭራ 5.9፣ ደብረ ማርቆስ 21.5፣ ፉኙዶ 4.5፣ ፍቼ 7.5፣ ጉንዶ መስቀል 6.0፣ ጋሳይ 9.5፣ ጋቲራ 14.7፣ 5.3፣ ጎሬ 10.5፣ ቡርጂ 16.2፣ ነቀምቴ 12.2፣ ሰዉላ 4.2፣ ሶኮሩ 5.7 ቴፒ 11.2፣ ወገልጤና 4.5፣ ቡልቂ 30.8፣ ጌጫ 14፣ ጅማ 14.0፣ ይርጋለም 12.0፣ 16.2፣ ሐሮማያ 5.3፣ ተርጫ 10.0፣ ወላይታ ሶዶ 5.0 እንዲሁም ደብራ ወርቅ 3.5 ሚ.ሜ የሚደርስ ከአነስተኛ እስከ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉዉ ወር በአስራ ሁለት (12) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ10 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ቀላል መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ ባለፈዉ የጃንዋሪ ወር በጥቂት የሀገሪቱ አከባቢዎች የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከ6-40 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛዉ በታች የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባሳለፍነው የጃንዋሪ ወር በተለይም በመጀመሪያውና በሁለተኛው አስር ቀናት ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አመዝኖ እንደነበር የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ለድህረ ሰብል እና ለእንስሳት መኖ ስብሰባ ተግባራትን በተሟላ መልኩ ለማከናወን በጎ ጎን ነበረው። በሌላ በኩል የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛው፣ የደቡብና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ አንጻራዊ ጥንካሬ እንደነበረውና ከአምስት ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ የተመዘገበ እንደነበር መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ በአንዳንድ ቅዝቃዜን መቋቋም በማይችሉ በመስኖ በሚለሙ የደጋ ሰብሎች፣ በቋሚ ተክሎችም ሆነ በጓሮ አትክልቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል የቅዝቃዜ ሁኔታ ተስተውሏል። በሌላ በኩል በተለይም በመጨረሻዎቹ አሥራ አንድ ቀናት በደቡብ ምዕራብና በተወሰኑ የደቡብ የሀገሪቱ ኪስ ቦታዎች ላይ የነበረው መጠነኛ እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በተወሰነ መልኩ አዎንታዊ አስተዋፅኦ የነበረው ሲሆን፤ በተጨማሪም የበልግ ወቅትን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው ጃንዋሪ ወር አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር እንደነበሩ የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ። ሆኖም በጥቂት የላይኛው ባሮ አኮቦ እና የመካከለኛው ኦሞ ጊቤ ተፋሰሶች መጠነኛ የገፀ ምድር እርጥበት የነበራቸው ሲሆን ይህም ሁኔታ ለውሃ ሀብት መሻሻል መጠነኛ አስተዋፅዖ እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ አይሻ፣ መረብ ጋሽ እና ኦጋዴን ተፋሰሶች የበጋው ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5) ።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1. መግቢያ

የፌብርዋሪ ወር በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ የሚጀምርበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የደቡብ ምዕራብ፣ ደቡብ፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የመካከለኛውና አጎራባች የስምጥ ሸለቆ ሥፍራዎች የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በመደበኛ ሁኔታ በፌብርዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚስተዋለው አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት በስተቀር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፈሎች ላይ ደረቃማው የአየር ሁኔታ ያመዝናል፡፡

### 1.1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ

የፌብርዋሪ ወር በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ የሚጀምርበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የደቡብ ምዕራብ፣ የደቡብ፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የመካከለኛውና አጎራባች የስምጥ ሸለቆ ሥፍራዎች የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በመጪው የፌብርዋሪ ወር የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ እና ለዝናብ መኖር ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በሰሜን ምሥራቅ፣ በምሥራቅ፣ በመካከለኛውና አጎራባች የስምጥ ሸለቆ ሥፍራዎች ላይ ከወሩ አጋማሽ በኋለ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

### 1.2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው ፌብርዋሪ ከወሩ አጋማሽ በኋላ የበልግ አብቃይ በሆኑት የደቡብ ምዕራብ፣ ደቡብ፣ ሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅ፣ መካከለኛውና የስምጥ ሸለቆ አጎራባች አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት የአፈር ውስጥ እርጥበት በመጠኑ ስለሚሻሻል የማሳ ዝግጅትን አስቀድሞ ለማከናወን የሚያስችል በመሆኑ፣ አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት አስፈላጊውን የዘር ግብዓት ከወዲሁ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የሚገኘው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውሃ አቅርቦት ምቹ

Ethiopian Meteorology Institute

ሁኔታ ከመፍጠሩም በላይ ለአርብቶ አደሮችና ለከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል።

## 1.3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው ፌብርዋሪ ወር በስምጥ ሸለቆ፣ በኦሞ ጊቤ፣ በገናሌ ዳዋ፣ እንዲሁም በላይኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የገፀ ምድር ውሃ ያገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት መሻሻል አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡

Ethiopian Meteorology Institute